የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት

የአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ

AFAR REGION DINKARA GAZETA

OF THE AFAR NATIONAL REGIONAL STATE

16ኛ ዓመት ቁጥር **51**
ሠመራ ቀን **2001** ዓ.ም

በአፋር ብሔራዊ ክልል መንግስት ምክር-ቤት
ጠባቂነት የወጣ

16th year No.51
Semera ------- 2009

ማውጫ

የአፋር ብሔራዊ ክልል ሠንደቅ አላማና ዓርማን ለመወሰን የወጣ አዋጅ ...ገጽ **1**

አዋጅ ቁጥር **51/2001** ዓ.ም

የአፋር ብሔራዊ ክልል ሠንደቅ አላማና ዓርማን ለመወሰን የወጣ አዋጅ

ከዚህ በፊት ክልሉ በሰንደቅ አላማና ዓርማ አሰቃቀል ረገድ ወጥነት የጎደለው አጠቃቀም የነበረ መሆኑ. በስራ ላይ ያለው ሰንደቅ ዓላማ የአፋር ህዝብ ለፍትህና ለዴሞክራሲ ስርዓት መስፈን ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ጋር በመሆን የከፈለውን መስዋዕትነትና የጀግንነት ታሪክ የተንፀባረቀበት ባለመሆኑ፣

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ም/ቤት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 3 እና ክልሉ ህገ መንግስት አንቀጽ 3 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የአፋር ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማና ዓርማን ለመወሰን የሚከተለውን አውጇል፣

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 51/2001 ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. <u>የአፋር ክልል ዓርማ</u>

ሁለት የተጠላለፉ ጊሌዎች ከላይ አናታቸው ላይ ባለ 5 ልሳን ቢጫ ኮከብ ኖሮት ሰንደቅ አላማው መካከል ላይ ያርፋል።

3. <u>የአፋር ክልል ሠንደቅ አላማ ቀለማት፣ አቀማመጥና መጠን</u>

የአፋር ክልል ሰንደቅ አላማ በአግድም የተሰመሩ 3 መደባት ሲኖሩት ከላይ ሰማያዊ፣ መካከሉ ነጭ ከታች አረንጓዴ ቀለማት ሲኖሩት ስፋታቸው እኩል መጠን ይኖረዋል።

ሰንደቅ አላማው ከግራ ጫፍ/ከላይና ከታችኛው/ ጀምሮ እስከ መሀል አንድ ሶስተኛ የሚሰመር ቀይ መልክ ያለው መደብ ሲኖረው ከጫፎቹ ላይ የሚነሳው መስመር አንድ ሶስተኛ ላይ ሲደርስ የሶስት ማዕዘን ቅርጽ ይኖረዋል።

ሰንደቅ አላማው የ 80 ሳ.ሜ ቁመትና የ 160 ሳ.ሜ ርዝመት ያለው ሆኖ ከጨርቅ የተዘጋጀ ይሆናል፡

4. <u>የሰንደቅ አላማው ትርጓሜ</u>

ሠማያዊው፡- ክልሉ የተፈጥሮ ፀጋ የሆኑ የተለያዩ የውሃ ሃብቶች እና ሌሎች እምቅ የተፈጥሮ ሃብቶችና መስህቦች መገኛ መሆኑን ያመላክታል።

ነጩ፡- የአፋር ክልል ህዝብ ሰላም ወዳድነትን እና ለሰላም የሚሰጠውን ትልቅ ዋጋ ያመለክታል።

ቢጫ ኮከብ፡- የአፋር ህዝብ ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ጋር በእኩልነት፣ በፍቅርና በመቻቻል መርህ እንደሚኖር ያመለክታል።

ቀይ መደብ፡- የአፋር ህዝብ ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦች ጋር በመሆን ለነፃነት፣ ለዲሞክራሲና ሰላም መስፈን የከፈለውን መስዋዕትነትና ጀግንነት ያመለክታል።

አረንጓዴው፡- የአፋር ክልልን ህዝብ የእድገት የብልፅግናና የልማት ራዕይን ያመለክታል።

5. <u>ሰንደቅ አላማው የሚሰቀልበት ጊዜ</u>

1. ስብሰባ በሚደረግበት አዳራሽ ወይም ሌላ ቦታ ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት፣

2. በትምህርት ቤቶች ትምህርት ከመጀመሩ በፊት፣

3. በቤተ-መንግስትና መንግስታዊ መስሪያ ቤቶች ከጠዋት 12፡00 ሠዓት እስከ ምሽቱ 12፡00

6. <u>የሰንደቅ አላማው የሚሰቀልበት ቦታ</u>

1. በቤተ መንግስት፣ በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በኮሌጆች፣ በዩኒቨርሲቲዎች፣ ህዝብ በሚሰበሰብበት ቦታና በስታዲዬም ወዘተ ------ ሲሆን ሰንደቅ አላማውም ከሌሎች ሰንደቅ አላማዎች ጋር አብሮ በሚሰቀልበት ጊዜ

ሀ. ከኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ አላማ ጎን በግራ በኩል ዝቅ ብሎ፣

ለ. ከሌሎች ፓርቲዎች ወይም ድርጅቶች ሰንደቅ አላማና ዓርማ ከፍ ብሎ ይሰቀላል።

7. <u>የሰንደቅ አላማው አሰቃቀልና አወራረድ ስነ- ስርዓት</u>

1. በት/ቤቶች ተማሪዎች በሚዘምሩበት የክልሉ መዝሙር ይሆናል።
2. በመንግስት መ/ቤቶች፣ በቤተ መንግስት ፣ በት/ቤቶች በፖሊስ ሠራዊት ካምፖች ወዘተ ---- ሰንደቅ አላማ ሲሰቀልና ሲወርድ ያጋጠመው ሰው በመቆም ክብሩን ይገልፃል።

8. <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

1. ሰንደቅ አላማውን በመናቅ ወይም በመጥላት መቅደድ ማቃጠል መልኩ እንዲቀየር ማድረግ ወይም መርገጥ በኢትዮጵያ የወንጀል ህግ ላይ በተደነገገው መሠረት ያስቀጣል።
2. ከዚህ ጋር የሚፃረር አዋጅ /ህግ/ ተቀባይነት የለውም።

9. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በአፋር ክልል ዲንካራ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የፀና ይሆናል።

እስማኢል አሊ ሴሮ

የአፋር ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት

ርዕሰ መስተዳድር